# የዝቅጠቱ ምልክቱ፣ ደበበ እሸቱ!

ራሔል ፍፁም

ስለ ደበበ እሸቱ ለመፃፍ መነሳት ራሱ የፖለቲካ ደዞታችን ምንኛ እንደዘቀጠ የሚያሳይ ነው ቢባል ስህተተ አይሆንም። ሰውየው ከመድረክ ቲያትረኝነቱ ባሻገር ለምን ከቁም ነገር ይገባል የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልሱ አዳጋች ይሆናል። ግን ያለንበትን የፖለቲካ ሁኔታ ደረጃ ለመጠቆም ይህ ግለሰብ በፖለቲካው መድረክ አለሁ ማለቱ ብቻ ሳይሆን ከተዋንያኑ ሁሉ ዋነኛው ነኝ ማለቱ ትችትን መጋበዙ አልቀረም። ይባስ ብለው ከግለሰቡ ተመሳሳይ ስራ ላይ የተሰማሩ ወይ የቲያትር ተጫዋቾችና ዘፋኞች ወይም ሯጮች የፖለቲካው አባወራ ነን ብለው ሲውገረገሩ ማየት የተገደደንበት ጊዜ መጥቷል። ስንተኛው ሺ ይሆን?

በአሁኑ ጊዜ ፖለቲካ ቀልድ የመሰላቸው ወይም ቀላል ከመ ገለባ ነው የሚሉ ጥቂት ናቸው አይባልም። በእርግጥ በዘፋኝነትና የመድረክ ተዋናይነት የተሰማሩ ለምን ፖለቲካ ገቡ ለማለት አይቻልም። በፖለቲካ ገብተው ለሀገራቸው ይዝፈኑ፣ተቃዋሚ ኃይሎችን ደርዱ ብንላቸውም ሆዳቸው ቀድሞባቸው ከወያኔ የሚያረገርጉትን አይተናልና። ፖለቲካ ብዙ ሩጫና ላብ ስላለበትም ሯጮችም እንግባበት ቢሉ የሚያስገርም አይሆንም። በሀገራችን ባይሆን በአሜሪካ ለምሳሌ በመድረኩ ችሎታቸው ፈዘዝ ያሉት እነ ሬጋንና ሽዋርዘንኤገር ወደ ፖለቲካው ገብተው በሚገባ አንቦጫርቀዋል። ደበበ እሸቱ በደጉ ዘመን ከተወዳጁ ከወጋየሁንጋቱ ጋር ሆኖ ሲያስቀን የነበር ሰው ነው። ኮሚክ የተባለ ማለት ነው። በፖለቲካ ኩምክና ግን የነበረው ችሎታ እምብዛም የታወቀ ሆነ የታየ አልነበረም። ደበበ ወደ ፖለቲካው ገባሁ ሲል ሕዝብን አሳዘነ አስቆጣ እንጂ አላሳቀም። የደርጉ ደጋፊ ሆኖ ደፋ ቀና ሲል፣ ኋላም የኢሰፓ አባል ሆኖ እዩኝ ሲል፣ ይህ የመድረክ ሰው ሊያስቅ ቀርቶ ፈገግም ሊያሰኝ ተስኖት ነበር። የሕዝብ መከራ አካል ሆኖ በመገኘቱ፣ ለፀረ ሕዝብ አገዛዝ ድጋፍ ሰጥቶ ጥብቅና በመቆሙ። ጊዜ አልፎ ሌላ ሁኔታ ሲከሰት ደግሞ ይህ ራሱን ወደ ፖለቲካ መድረክ አውጥቶ ያዋረደ ግለሰብ ድምፁን አጥፍቶና ሕዝብን ይቅርታ ጠይቆ መገኘት ሲገባው እንደገና ወደ ፖለቲካው ዘው በማለት ብዙዎችን ባሳቀና ኋላም ባስቆጣ መልክ የቅንጅት አመራር ኮሚቴ አባል ሆኖ ብቅ አለ ። አመራር ? ቅንጅት ዛሬ ያለበትን አሳዛኝ ሁኔታ ስንመለከት ምናልባትም የነ ደበበ ዓይነቱ መሪዎች መሰየማቸው የችግሩ ምክንያት ሆኖ ይሆን ብሎ መጠየቅ እንገደዳለን። ዛሬ ደበበ ቅንጅትን ራሱን እየተቸና እከሳለሁ እያለ ከማስፈራራት አልፎ ኢሕአፓና መኢሶንንም ሕዝብን ይቅርታ ጠይቁ ብሎ መካሪም ወቃሽም ሆኗል።

የዝቅጠቱ ምልክት የሆነው ደበበ በመድረክ ዋና ቦታን ይዞ መገኘቱ፣ በፖለቲካው መስክ ድምፃቸው ቃና ቢስ ችሎታቸው ደግሞ ኢምንት የሆኑ ዘፋኞችም አለና አለና ማለታቸው፣ ዝነኛ አትሌት/ሯጭ ስለተባለ ብቻ በፖለቲካው መስክ በአፍቅሮ ወያኔ መስመር ከዚያ መዘዘኛ ፕሮፌሰር ይስሐቅ ጋር ሰበር ሰካ የሚለው ግለሰብ አስታራቂ መባሉ ሁሉም የሚያሳየውን ምንኛ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደዘቀጠ ወይም እንደ አሽቅለቆለ ነው። የትላንቱ ሀቅ በደፈናው ተረስቶ ያኔ ከገዳይ ጋር ጉሮ ወሸባዬ ሲሉ የነበሩት ዛሬ ተቃዋሚ ነን ብለው ከመኮፈሳቸው አልፈው በተገደሉት ወገኖችና ቀሪዎቹ ላይ ሲያቅራሩ ዝም ብሎ ማየቱ ስለተለመደ ነገር ሁሉ ብልሽትሽት እያለ ነው። ያለንበት ጊዜ በእርግጥ በፓል ቶክ ደረጃ አርበኛ የሆኑ ግለሰቦች "ብዙ ምሰዋዕትነት ከፍለናል በዚህ መድረክ!" ብለው የሚኩራሩበትና አይ ፖድ በቃሊቲ ይዘው የሚዝ ኑ የፖለቲካ እስረኞች የታዘብንበት ወቅት ነው። ተገለባብጧል ነገር ዓለሙ ሁሉ። በወያኔ እስር ቤት ተኩኖ የ 600 ገፅ መፅሐፍ ፅፎ ማውጣትና ማሳተምም ተችሏል። የቀይ ሽብር ወንጀለኞችም በፓልቶክ አስተዳዳሪ ሆነው "ምዕመናኑን" አስተማሪ ሆነው በራሳቸው ተሰይመዋል። ማነው ሀገር ወዳድ፣ ማነው አስመሳዩ፣ ማነው ይባስ ብሎስ ከአራጆች ጋር የተመሳጠረ? ብለን ብንጠይቅ ነገሩ ዝብርቅርቅ ሆኗል። በመሆኑም ከማን አንሼዎች ፈልተዋል። የሚጀምር ጠፍቶን እንጂ ምንም ሳይማሩ ቀዶ ጥገና ሞካሪዎችም ብቅ ብቅ ባሉ ነበር። የሐረሩ ተሳንጪ ሊቀመንበር፣መጋቢ ሀምሳ አለቃ ረዳቱ ሆነው ሀገርን ለ17 ዓመት ካደሙ እነ ተፈራ ዋልዋና አዲስ ዓለም ባሌማስ ለምን ይሳቅባቸዋል? ትላንት በሕዝብ የተወገዙና የሰው ሚስት ለመቀማት ስልጣነቸውን ተጠቅመው፣ ከመንግሰቱ ተጠግተው ባሎችን ያሳደዱና የገደሉ ዛሬ በዋሽንግተን አንቱ ከተባሉ ጋሼ ደበበስ የፖለቲካ መሪ ነኝ ብቻ ሳይሆን ከእኔም በላይ ለአሳር ብለው ቢኩራሩ ለምን እንገረማለን? በተለምዶ እምባጮ ለታቦት የሚቆረጠው ክቡሩ አንጬት ሲጠፋ ነው። በፖለቲካው መስክ ግን አዋቂዎቹ ሳይጠፉ አላዋቂዎቹ መድረክ አጨናንቀው አላናግር አላሰራ አሉ። አቶ ደበበ አንኳን ያቺን መከረኛ ዶክተር ፕሮፌሰር ኢንጂነር ቅፅል ከስሙ ፊት ለጠፍ አላደረገም። በዚህ ረገድ ቅፅል ተሸክመው ቅል ራስ ከሆኑት አሳፋሪ ፍጡሮችና የወያኔ ሎሌዎች ምንም የምጠብቀው የለም የሚል መምሰሉ ባናውቀው ለምስጋና ዕጩ ያደርገው ነበር። ግን የአቶ ደበበ ድፍረት የአላዋቂ ነው። የሌባ ዓይነ ደረቅ ብጤ። ቀደም ሲል ለወያኔም ደፋ ብሎ ነበር ተበሎ ታምቷል። ተቃዋሚ ነኝ ታሰርኩ ካለ በኋላ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ደግሞ ቤቱ እየተኛ ፣ ቃሊቲ የተመዘገበውን አጅቦ አሁንም ከወያኔ ልቀራረብ ባይ ነው። ታጥቦ ጭቃ ሳይሆን ሳይታጠቡ ወደ አዲስ ማጥ መግባት የተሻለ ይሆናል።

በተወሰነ ደረጃ ቢሆንም ለዚህ ሁሉ ደበባዊ ዝቅጠት ተጠያቂ በተለይ በውጭ ሀገር ያለው ኢትዮጵያዊ መሆኑን መቀበል ያስፈልጋል። በውጭ ሀገር ያሉ ወገኖች አላፊ አግዳሚውን ሆ! ብለው ለማድነቅና ለመማማዳነቅ ጊዜ አይፈጅባቸውም። ከልደቱ ብቻ መነሳት ይቻላል። ከእሱ በፊት ኮለኔል ጎሹ “የደርጉ” ወልዴ ታጋይ ተብሎ ሲወደስ ሲሰገድለት ነበር--- አንዲት ቀን እንኳን ይቅር በሉኝ ሳይል!! የደርጉ የጦር ፍርድ ቤቱ መሀል ዳኛ፣የኢሰፓ ማኮ አባልና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር። ልደቱም ገና ብቅ እንዳለ ማንዴላ ተባለ! ሰላይና አስመሳዮች ታስረውና ተደብድበው ተመሳስለው እንደሚያወናብዱ እያወቅን ወር በመታሰሩ (ያውም ሳይደበደብ) ማንዴላ መባሉ ያስከተለውን ውዝንብር የምናውቀው ነው ዛሬ። ፕሮፌሰር ይስሐቅም ጎህ ሲቀድ ሲሞገስ ነበር--እንደዛሬ አያድርገውና ማለት ነው። ወንጀለኞች ንስሃ እንዲገቡ መጠየቃቸው ተገቢ ነው። ቀልቤሳ የተቃዋሚ መሪ ሊባል ነበር? ኦነግ የተባለውን ስብስብ እያጨናነቁ ያሉት ወንጀለኞች ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። የአርባጉጉው አሊ ሀሰን። ያቺ አልማዝ መኮ። የ ፀሀንን ደም ያፈሰሱ ጀግና ተብለው ሲመሰገኑ መታዘቡ መቆም አለበት ማለት ነው። አይደረግም፣ ይቁም ማለት መቻል ይኖርብናል። በአጭሩ ንፁህ ማለቱ በፖለቲካ አወዛጋቢ ሊሆን ቢችልም ግን የፖለቲካ ደላላዎች ወይም በቅርቡ አንድ ተቺ እንዳስቀመጠው ወያላዎች ከመድረኩ ራቅ **ቢሉ** ይመረጣል። **ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ እየሆን 17 ዓመት ሙሉ ካጋጠመን ቁጭ በሉ ልንማር ይገባል።**

የደበበ እሸቱ ይቅርታ ጠይቁ ልፈፋ ሆነ ቅንጅትን እከሳለሁ ድንፋታ ሰውየው ዓይን አውጣ ኮሚክ መሆኑን የሚያረጋግጥለት ነው። በስራው በስምሪቱ ሊቆይ ቢችል ይሻል ነበር። ያለፈ ታሪኩን ከዛሬው ዝቅጠቱ አያይዘን በመተቸት ወረቀት እንድንጨርስ ባይጋብዘንም ደግ። ሌሎችም እንዲሁ ሊመከሩ ይገባቸዋል። ፋራና ጢስ መውጫ አያጡም ስለተባለ ዓይንን በጨው አጥቦ ፖለቲውን ማተራማረስ ከጥቅሙ ዜሮ ፣ ከጉዳቱ መቶ ነው። ደበበ እሸቱ ሚናው በዚህ መልክ ይፈረጃል። ሀይ ሀይ የሚሉትም የዚሁ ተባባሪ ናቸውና ቢያንስ መጠንቀቅ ይገባቸዋል። ብንታደል ኖሮ ደበበ እሸቱ የፖለቲካ መሪዎቻችንን እያሳቀና እያዝናና ለጠነከረ ስራ ባበረታታቸው ነበር። ግን አልሆነም። ክቡር ስራውን ትቶ ወደ “ፖለቲካ” ገብቶ ፖለቲካን ገደል ከተተ፣አቆሸሸ። ደበበ እሸቱ ፖለቲካኛ? ቅ ቅ ቅ ቅ ቅ ቅ ቅ !!!!!!

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com